# ተው ተመለስ ባንዳ! ለሰላሳ ዲናር አትሁን ይሁዳ!




ነገ ሊቀር ዓለም ለሚፈርስ ገላ፣
በሆድህ ተገዝተህ ትራፊ ልትበላ፣
ለልጅ የልጅልጆች አትሁን ማፈሪያ፣
ተው ስማ ተመከር ተው ተመለስ ባንዳ!

ውርደት ሆዳምነት ቢመዘን ቢለካ፣
ከይሁዳ ሳጥናኤል ተጭራቅ የከፋ፣
ባንዳ እንደ አንተ አለ ወይ እጅጉን የከዳ?

ከርስህን አስፍተህ እንደ ስንዴ ኬሻ፣
ጅራትህን ወትፈህ ተጭራቆች ጉያ፣
ወገን አታስነክስ ባንዳ ልብ ግዛ!

መሞት ላይቀርልህ በእድሜ በበሽታ፣
መብል አስጎምጅቶህ የባሰም ተአሳማ፣
ወገንህን ለሚያርዱት አትሁን እጀታ፣
እስቲ አሞት ይኑርህ ባንዳ ልብ ግዛ።

የምትኖራት እድሜ ሰማንያ ላትሞላ፣
ታሪክ አይርገምህ ዘላለም ጧት ማታ፣
ተው ንስሀ ግባ አቁም! ይብቃህ! ባንዳ!

እንደ ፈረንጅ ኬሻ ለመሙላት ከርስህን፣
ለአሰስ ለገሰሱ ለምን ሎሌ ትሆን?

ከምሳር እጀታ ከዛቢያውም ከፍተህ፣
ህጻናት ተሚያርዱት ኩምቢህን ወትፈህ፣
ዘመድ ወገንህን ያሳጨድክ ያስቆረጥክ፣

ምድር ተሰንጥቃ ወደ ውስጥ ታስምጥህ፣
ሰማይ ቋያ ሆኖ እንደ እሳት ያንድህ!

እንደ አምስቱ ዘመን እንደ አድዋው ባንዳ!
ሞተህ አፈር ልትሆን ከመቃብር ዋሻ፣
ምስጥ እንክት ሊያደርግህ እስክትሆን ትቢያ፣
ጭራቅ ሎሌው አርጎህ ወገን አታስበላ፣
ተመልሰህ ሰው ሁን ባንዳ ልብ ግዛ።

ለሰላሳ ዲናር አትሁን ይሁዳ!
ንስሀ ግባና ተአርበኞች ጋር ሥራ፣
ተእግራቸው ተደፍተህ ፋኖን በል ይቅርታ፣
ተመከር ተዘከር ተው ተመልስ ባንዳ!

በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)
መስከረም ሁለት ሺ አስራ ስድስት ዓ.ም.